# በትራንስፖርት ሚኒስቴር

# የመድን ፈንድ አስተዳዳር ኤጀንሲ የተሽከርካሪ አደጋ ተጐጂ የአስቸኳይ ህክምና አገልግሎት አፈፃፀም መመሪያ ቁጥር 655/2013

## /ማሻሻያ/

በትራንስፖርት ሚኒስቴር የመድን ፈንድ አስተዳደር ኤጀንሲ የተሽከርካሪ አደጋ ተጐጂ የአስቸኳይ ህክምና አገልግሎት መመሪያን ማሻሻል አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ በተሽከርካሪ አደጋ የሶስተኛ ወገን መድን አዋጅ ቁጥር 799/2005 አንቀፅ 29(2) እና መመሪያው አንቀፅ 42 መሠረት እንደሚከተለው ተሻሽሏል፡፡

1. አጭር ርዕስ
   - ይህ መመሪያ በትራንስፖርት ሚኒስቴር የመድን ፈንድ አስተዳደር ኤጀንሲ የተሽከርካሪ አደጋ ተጐጂ የአስቸኳይ ህክምና አገልግሎት አፈፃፀም መመሪያ ቁጥር 655/2013 "ማሻሻያ" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

2. ማሻሻያ

   በትራንስፖርት ሚኒስቴር የመድን ፈንድ አስተዳደር ኤጀንሲ የተሽከርካሪ አደጋ ተጐጂ የአስቸኳይ ህክምና አገልግሎት አፈፃፀም መመሪያ ቁጥር 655/2013 እንደሚከተለው ተሻሽሏል፡፡

   (1) የመመሪያው አንቀፅ 21 ንዑስ አንቀፅ (1) ተሠርዞ በሚከተለው አዲስ ንኡስ አንቀፅ (1) ተተክቷል፡፡

   21(1) የተዘዋዋሪ ፈንዱ ከመድን ሰጭ ኩባንያዎችና ከመድን ፈንድ አስተዳደር ኤጀንሲ የሚሰበሰብ ወርሃዊ መዋጮ ነው፡፡

   (2) የመመሪያው አንቀፅ 21(2) ተሠርዞ በሚከተለው አዲስ አንቀፅ 21(2) ተተክቷል፡፡

   21(2) የመድን ሰጭ የመዋጮ ድርሻ የሶስተኛ ወገን የተሽከርካሪ አደጋ የመድን ዋስትና የአረቦን መጠንና የመድን ፈንድ ታሪፍ በተጠናውና በሚንስትሮች ምክር ቤት መጋቢት 10 ቀን 2003 ዓ.ም. በፀደቀው መሠረት 3% ይሆናል፡፡

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የትራንስፖርት ሚኒስቴር
The Federal Democratic Republic of Ethiopia Ministry of Transport

(3) በመመሪያው አንቀፅ 21(3) ላይ አዲስ ንኡስ አንቀፅ (3)(ሐ) ተጨምሯል፡፡

21(3)(ሐ) በአረቦን መጠንና የመድን ፈንድ ታሪፍ ጥናት መሰረት ተደርጎ በየወሩ ከመድን ሠጭ ኩባንያዎች ከሚሠበሠበው ተዘዋዋሪ ፈንድ ላይ ጨምሮ በጤና ሚኒስቴር በተከፈተው የባንክ ሂሳብ ውስጥ ገቢ ማድረግ አለበት፡፡

(4) የመመሪያው አንቀፅ 22 ተሠርዞ በሚከተለው አዲስ አንቀፅ 22 ተተክቷል ፡፡

22/ የተዘዋዋሪ ፈንድ መጠንና ገቢ የሚደረገው የመዋጮ ድርሻ ገቢ የሚሰበሰበው ኤጀንሲው በሚያደርገው ጥናት ላይ ተመስርቶ የሚንስትሮች ምክር ቤት በወሰነው የአረቦን ጥናት መሠረት እ.ኤ.አ.(Gregorian Calendar) የቀን አቆጣጠር በየወሩ ሆኖ ወሩ ባለቀ በሚቀጥለው ወር የመጨረሻ ቀን ድረስ ነው፡፡ የቀጣዩ ወር መጨረሻ ቀን ዕሁድ ወይም የበዓል ቀን ከሆነ የመጨረሻው ቀን ቀጣዩ የስራ ቀን ይሆናል፡፡

(5) የመመሪያው አንቀፅ 23 ተሠርዞ በሚከተለው አዲስ አንቀፅ 23 ተተክቷል፡፡

23/ ኤጀንሲው በዚህ መጠን የተሰላውን የአረቦን ጥናት መንግስት ውሳኔ በሰጠ በ3 የስራ ቀናት ውስጥ ለሚመለከታቸው አካላት በጽሁፍ ያሳውቃል፡፡

(6) የመመሪያው አንቀፅ 24(1) ተሠርዞ በሚከተለው አዲስ አንቀፅ 24(1) ተተክቷል፡፡

24(1) ለተዘዋዋሪ ፈንድ የመዋጮ ድርሻ ገቢ የሚደረጉ ክፍያዎች በኤጀንሲው ስም በሚከፈት የባንክ ሂሳብ ሆኖ በኤጀንሲው አማካኝነት ለዚሁ ተብሎ በጤና ሚኒስቴር በተከፈተው የባንክ ሂሳብ ውስጥ ገቢ ይደረጋል፡፡

(7) የመመሪያው አንቀፅ 24(2) ተሠርዞ በሚከተለው አዲስ አንቀፅ 24(2) ተተክቷል፡፡

24(2) በአንቀፅ 21(1) መሰረት የአረቦን መጠንና የመድን ፈንድ ታሪፍ በሚኒስትሮች ምክር ቤት በተወሠነው መሠረት በመድን ፈንድ አስተዳደር ኤጀንሲ በተከፈተው የባንክ ሂሳብ ውስጥ እ.ኤ.አ. (Gregorian Calendar) የቀን አቆጣጠር በየወሩ ሆኖ እያንዳንዱ ወር ካበቃ በኋላ ባለው ቀጣይ ወር መጨረሻ ቀን ድረስ ሁሉም መድን ሠጭ ኩባንያዎች ገቢ ማድረግ አለባቸው፡፡ የቀጣዩ ወር የመጨረሻ ቀን ዕሁድ ወይም የበዓል ቀን ከሆነ የመጨረሻው ቀን ቀጣዩ የስራ ቀን ይሆናል፡፡

(8) የመመሪያው አንቀፅ 24(3) ተሠርዞ በሚከተለው አዲስ አንቀጽ 24(3) ተተክቷል፡፡

24(3) በዚህ አንቀፅ ንኡስ አንቀፅ (2) በተጠቀሰው የክፍያ ወቅት ውስጥ የሰበሰበውን የተዘዋዋሪ ፈንድ ታሪፍ ገቢ ያላደረገ የመድን ሠጭ ኩባንያ ክፍያውን ላዘገየበት ጊዜ የዘገየው የገንዘብ መጠን ላይ በኢትዮጵያ የፍትሐብሔር ህግ ውስጥ የተደነገገውን ህጋዊ ወለድ ጨምሮ በኤጄንሲው የባንክ ሂሳብ ውስጥ ገቢ የማድረግ ግዴታ አለበት፡፡

(9) የመመሪያው አንቀፅ 26(1)(ሀ) ተሠርዞ በሚከተለው አዲስ አንቀፅ 26(1)(ሀ) ተተክቶል፡፡

26(1)(ሀ) በአጠቃላይ በሦስተኛ ወገን የተሽከርካሪ አደጋ የመድን ዋስትና የአረቦን መጠንና የመድን ፈንድ ታሪፍ የተጠናው የተዘዋዋሪ ፈንድ ከሚሠጠው የአስቸኳይ ህክምና አገልግሎት ክፍያ አንፃ ሲገኝ የመድን ፈንድ አስተዳደር ኤጀንሲ በሚያደርገው ጥናት ላይ ተመስርቶ ቦርድ በሚወስነው መሠረት ማስተካከያ ይደረጋል፡፡

(10) የመመሪያው አንቀፅ 26(1)(ለ) ተሠርዞ በሚከተለው አዲስ አንቀፅ 26(1)(ለ) ተተክቷል፡፡

26(1)(ለ) የተጨማሪ አጠቃላይ የተዘዋዋሪ ፈንድ ተመኑ በመድን ፈንድ አስተዳደር ኤጀንሲ በሚጠናው የአረቦን መጠን እና የመድን ፈንድ ታሪፍ መሠረት ተደርጉ ቦርዱ በሚወስነው መሰረት ይሆናል፡፡

(11) የመመሪያው አንቀፅ 26(1)(ሐ) ተሠርዞ በሚከተለው አዲስ አንቀፅ 26(1)(ሐ) ተተክቷል፡፡

26(1)(ሐ) በዚህ መጠን የተሠላው አጠቃላይ የተዘዋዋሪ ፈንድ ተመን የሦስተኛ ወገን የተሽከርካሪ አደጋ የመድን ዋስትና የአረቦን መጠን እና የመድን ፈንድ ታሪፍ ስሌት በተወሰዱ መለኪያዎች መሠረት ይሆናል፡፡

(12) የመመሪያው አንቀፅ 26(1)(ሠ) ተሠርዞ በሚከተለው አዲስ አንቀፅ 26(1)(ሠ) ተተክቷል፡፡

26 (1)(ሠ) የዚህን የመዋጮ ድርሻ ኤጀንሲው በደብዳቤ ባሳወቀ በ5 የስራ ቀናት ውስጥ በኤጀንሲው በተከፈተ የባንክ ሂሳብ ውስጥ ገቢ ማድረግ አለባቸው ኤጄንሲውም ከሁሉም የመድን ሠጭ ኩባንያዎች የሠበሰበውን የተዘዋዋሪ ፈንድ መዋጮ የራሱን ድርሻ ጨምሮ



The Federal Democratic Republic of Ethiopia Ministry of Transport

በ5 የስራ ቀናት ውስጥ ለዚሁ በተከፈተ የጤና ሚኒስቴር የባንክ ሂሳብ ውስጥ ገቢ ማድረግ አለበት።

(13) የመመሪያው አንቀፅ 26 (2) (ሀ) እና (ለ) ተሰርዘዋል ።

3. <u>መመሪያው የሚፀናበት ጊዜ</u>

- ይህ መመሪያ በኢ.ፌ.ዴ.ሪ. የትራንስፖርት ሚኒስቴር ሚኒስትር ተፈርሞ ከወጣበት ዕለት ጀምሮ የፀና ይሆናል።

ዳግማዊት ሞገስ

የትራንስፖርት ሚኒስቴር ሚኒስትር